በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 247153 እና 245689

ህዳር 05 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

በሰ/መ/ቁ.247153

አመልካቾች፡- 1ኛ. አቶ አህመድ የሱፍ --------- ቀረበ

2ኛ. ወ/ሮ ሃያት ኢብራሂም -- አልቀረበም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጥሩ አለም ጌጡ ------ ቀረቡ

በሰ/መ/ቁ.245689

አመልካች፡- ወ/ሮ ጥሩ አለም ጌጡ ----- ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1ኛ. አቶ አህመድ የሱፍ ----- ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ሃያት ኢብራሂም ------ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 11/09/2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የባህር ዳር ከተማ ወረዳ ሽሪአ ፍ/ቤት በመ.ቁ.58562 በቀን 27/07/2014 ዓ.ም ሰጥቶት የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ የሸሪአ ፍ/ቤት በመ.ቁ.0331123 በቀን 15/10/2014 ዓ.ም የጸናውን ውሳኔ የአ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት በመ.ቁ.59199 በቀን 22/03/2015 ዓ.ም በመሻር መወሰኑ እና የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.119939 በቀን 24/06/2015 ዓ.ም አሻሽሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለታቸው ሲሆን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ ሆነው 1ኛ አመልካች ተከሳሽ ሆነው እንዲሁም 2ኛ አመልካች ጣልቃ ገብ ሆነው በባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በቀን 22/01/2012 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ ከ1ኛ አመልካች ጋር ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ጋብቻ የነበራቸውና በጋብቻው ውስጥም ሶስት ልጆች የወለዱ መሆኑን በመግለጽ ጋብቻው እንዲፈርስ፣ የልጅ ቀለብ እንዲቆረጥላቸው እንዲሁም 1ኛ. በባህር ዳር ከተማ የሚገኝ ሚና ዱቄት ፋብሪካ፣ 2ኛ. በሞጣ ከተማ የሚገኝ ስኬት ዱቄት ፋብሪካ 3ኛ. ሃቂቃ ማህበር 4ኛ. NMH ማህበር 5ኛ. በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኝ ማህበር 6ኛ. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፣ በቡና ባንክ ፣ በወጋገን ባንክ የሚገኙ ሀብቶች የጋራ በመሆናቸው ያካፍለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ አመልካችም በ25/02/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ጋብቻው የተመሰረተው ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እንጂ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ አይደለም በማለት ልጆች ግን መውለዳቸውን አምነው ንብረትን በተመለከተ ሚና ፋብሪካ ከሚባለው ድርጅት ድርሻ የለኝም፡፡ ስኬት የተባለው ፋብሪካ ተጠሪን ከማግባቱ በፊት የተገዛ በመሆኑ ተጠሪን አይመለከታትም፡፡ NMH ማህበር ተሸጦ ተጠቅመንበታል፡፡ በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኝ ማህበር የለኝም፡፡ በባንኮች ውስጥ አለ የተባለውም ገንዘብ የለኝም፡፡ የቀረበው ንብረትም ግምቱ የተጋነነ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከዚህ በኋላ 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት አቤቱታ 2ኛ ተጠሪ እና አይሻ ዳውድ የምትባል የ1ኛ አመልካች ሚስት ያለ መሆናቸውን በመግለጽ ስኬት የዱቄት ፋብሪካ በመካከላቸው ሊካፈል የሚገባ ነው በማለት አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ወ/ሮ አይሻ ዳውድ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ መጥሪያ ቢልክም ለመከራከር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በ1ኛ አመልካች በኩል ገልጸዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ከሚመለከታቸው አካላት ስለ ንብረቶቹ ማስረጃ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ በሚና የዱቄት ፋብሪካ፣ በሞጣ ከተማ ከሚገኘው ስኬት የዱቄት ፋብሪካ፣ የአውሳ ሪል ስቴት ማህበር፣ NMH ማህበር የሚገኙት ንብረቶች ላይ 1ኛ አመልካች ድርሻ ያለው መሆኑ በመረጋገጡ ከዚሁ ንብረት ላይ የአመልካቾች ድርሻ ግምት ውስጥ ገብቶ ተጠሪ 1/3ኛ ድርሻ የሚገባት በመሆኑ ከተቻለ በስምምነት ይካፈሉ ካልተቻለ ተሸጦ ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት ለባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን አመልካቾችም መስቀለኛ ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ አጣምሮ የስር

ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አለን በማለት ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት አቤቱታ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ማጽናቱን ተከትሎ ለአ/ብክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ችሎቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የስር ፍ/ቤት በተጠሪ በኩል የቀረቡ የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ በግራ ቀኙ የተቆጠሩ ምስክሮችን ሳይሰማ ከተቋማቱ የቀረበውን ማስረጃ ብቻ መሰረት በማድረግ መወሰኑ የክርክር አመራር ህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ተገቢውን ሊወስን ይገባል በማለት መዝገቡን ለስር ፍ/ቤት ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

መዝገቡ የተመለሰለት የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ጋር ከመረመረ በኋላ በባህር ዳር ከተማ የሚገኘውን ሚና አክሲዩን ማህበር እና በሞጣ ከተማ የሚገኘውን የዱቄት ፋብሪካ በተመለከተ በ1ኛ አመልካች ስም ያለውን ድርሻ ተጠሪና አመልካቾች እኩል ሊካፈሉ ይገባል፡፡ በባህር ዳር ከተማ የሚገኘውን አውሳ ሪል ስቴት እና ሀቂቃ አክሲዩን ማህበርን በተመለከተ ተጠሪ ልትጠይቅ አይገባትም፡፡ የNMH ማህበርን በተመለከተ የ1ኛ አመልካችን ድርሻ ሶስቱም እኩል ሊካፈሉ ይገባል፡፡ 1ኛ አመልካች ከአዋሽ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ አለብኝ ያለውን እዳ በተመለከተ ተጠሪ ልትጠየቅ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾችም ተጠሪም በየበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮብኛል በማለት ለባህር ዳር እና አካባቢዋ ከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ሌላውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት አውሳ እና ሀቂቃ ማህበሮችን በተመለከተ አመልካች መኖራቸውን ስላልካደ የስር የባህር ዳር ወረዳ ሸሪአ ፍ/ቤት የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አስቀርቦ አረጋግጦ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ ይመለስለት በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች እና ተጠሪ በተለያየ መዝገብ በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ አለኝ በማለት ለአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቦቹን አጣምሮ ከመረመረ በኋላ የስር የወረዳ ሸሪአ ፍ/ቤቱ የ1ኛ አመልካች ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል እርስ በርሱ የሚጣረስና ተዘርዝሮ ከቀረበው የጋራ ሀብት ጋር ግንኙነት የሌለው መሆኑ እየታወቀ በቂ የማስረጃ ምዘና ሳያደርግ የሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው ነው ብሎ በመሻር ሚና ዱቄት ፋብሪካና በሞጣ ከተማ የሚገኝ ስኬት ዱቄት ፋብሪካ የተመሰረተው በ1ኛ አመልካች ስም በመሆኑ የሁለቱ ፋብሪካዎች ግምት ብር 25,000,000 (ሃያ አምስት ሚሊየን) 1ኛ አመልካች 1/3ኛውን ለተጠሪ ያካፍሉ፡፡ ከተራ ቁጥር 3-5 ተገምተው የቀረቡት አክሲዮኖች ላይ ከ1ኛ አመልካች ድርሻ 1/3ኛውን ለተጠሪ ያካፍሉ፡፡ በስር ፍ/ቤት በባንክ የተገኘ ገንዘብን በተመለከተ የተጣራና የተገኘ ገንዘብ ስለሌለ ታልፏል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾችም በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታ አለን በማለት ለአ/ብክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ችሎቱ ከመረመረ በኋላ ሚና ትሬዲንግ እና ሞጣ ከተማ የሚገኝ ስኬት

ዱቄት ፋብሪካ ከንግድ ቢሮ በተረጋገጠው መሰረት አክሲዮኖች መሆናቸው ተረጋግጦ እያለ ምስክሮች 1ኛ አመልካች ሲያቋቁመው እናውቃለን በማለታቸው ብቻ የጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤቱ እነዚህ ንብረቶች የ1ኛ አመልካች የግል ሀብት ናቸው ብሎ መደምደሙ ተገቢ ባለመሆኑ ተሽሯል፡፡ በእነዚህ ንብረቶች ረገድ የወረዳው የሸሪአ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ ሌላው የጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ጸንቷል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾችም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ11/09/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ሚና ትሬዲንግ እና የሞጣ ስኬት የዱቄትና የፓስታ ፋብሪካ 1ኛ አመልካችና ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት የተፈራ ንብረት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ መብት ሊኖራት አይገባም፡፡ መብት አላት የሚባል ከሆነም ከ1ኛ አመልካች ድርሻ መሆን ሲገባው እኩል ለ3 ይካፈሉ ተብሎ መወሰኑ፤ የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት ከተራ ቁጥር 3-5 ተዘርዝረው የቀረቡትን 1/3ኛ ያካፍሉ በማለት የወሰነበት ላይ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰው ሃቂቃ ማህበር ሲሆን በዚህ ማህበር በ1ኛ አመልካች ስም የአክሲዩን ድርሻ የለም በማለት እየተከራከርኩ ድርሻ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተብሎ መወሰኑ፤ NMH ማህበርም የተሸጠ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተካፈሉ መባሉ፤ ለስኬት የዱቄት ፋብሪካ የማሽን ግዥ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ከአዋሽ ባንክ በማህበር ደረጃ የብድር እዳ መኖሩ ተረጋግጦ ባለበት ተጠሪ የድርሻዋን እዳ መክፈል እያለባት መታለፉ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎት አመልካቾችን በሚሰማበት ወቅት አመልካቾች በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ሼህ አብዱ ሀሰን የተባሉት ዳኛ ቅሬታ እያቀረብን በከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት እና በጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት በሁለት የተለያዩ እርከን ላይ በሚገኙ ፍ/ቤቶች ተሰይመው ጉዳያችንን ተመልክተው መወሰናቸው ተገቢ አይደለም የሚል አቤቱታ ማቅረባቸውን ተከትሎ መዘገቡን አይቶ ይኸው ነጥብ በሰበር ሰሚው ችሎት ሊጣራ ይገባል ብሎ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ መርቷል፡፡ ይህ ችሎትም ጉዳዩን ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ መሰረት ተጠሪ በ19/10/2015 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ የከፍተኛ ሸሪአ ፍ/ቤት ዳኛ የሆኑት ዳኛ ሼህ አብዱ ሀሰን ከስር የጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት ዳኞች አንደኛው በጡረታ ከስራቸው በመነሳታቸው የዚሁን ዳኛ ቦታ ደርበው በጊዜያዊነት እንዲሰሩ በአ/ብ/ክ/መ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተወከሉ በመሆኑና ይህም በሸሪአ ፍ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ የሚፈቀድ በመሆኑ ዳኛው ተሰይመው ውሳኔ መስጠታቸው ተገቢ ነው፡፡ አመልካቾችም ዳኛ ተተክቶ ጉዳያችን ይታይ ብለው በጠበቃቸው አማካኝነት ጠይቀውና ተስማምተው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አሁን ተቃውሞ እያቀረብን በማለት ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም፡፡ ከስር ጀምሮ እስከ አሁን እየተከራከረ ያለው የአመልካቾች ጠበቃ አንድ ሰው ሆኖ እያለ በጠበቃቸው አማካኝነትም ሆነ በራሳቸው በዳኛ አሰያየም ጉዳይ በስር ፍቤቶች ተቃውሞ ሳያቀርቡ ቆይተው አሁንም የህግ ባለሙያ ባለመሆናችን በጽሁፍ አቤቱታችን

አላካተትነውም ማለታቸው ተገቢነት የሌለው እና አሁን ሊያነሱት የማይገባው መቃወሚያ በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናልኝ እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም በ29/10/2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታቸውን አጠናክረዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ተጠሪ በመ.ቁ. 245659 የስር የስር የአብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በ02/08/2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፦ ሚና ዱቄት ፋብሪካና በሞጣ ከተማ የሚገኘው ስኬት ዱቄት ፋብሪካ የ1ኛ አመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ባቀረብኳቸው ምስክሮች ከአመልካቾች በተሻለ ሁኔታ አስረድቼ እያለ የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ሳይኖረው ንብረቱ የአክሲዩን ነው በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት በመሆኑ ተሽሮ እነዚሁ ንብረቶች የባልና ሚስቱ ናቸው ተብሎ 1/3ኛ እንድንካፈል እንዲወሰንልኝ እጠይቃለው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሽሪአ ጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሳኔ የሻረበት አግባብነት መጣራት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ተጠሪ ጉዳያቸው በዚህ መዝገብ ከቀረበው የአመልካቾች አቤቱታ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ አቤቱታ አቅርበው ችሎቱም ሁለቱም ጉዳዮች ከአንድ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የመነጩ መሆናቸው በመረጋገጡ የተጠሪ አቤቱታ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶበት፤ከዳኛ አሰያየም ጋር በተያያዘ ለቀረበው ክርክር አመልካቾች ሊያቀርቡት የሚችሉት መልስ በሰ/መ/ቁ.245173 ካቀረቡት ቅሬታ ጋር የሚመሳሰል በመሆኑ ሊጣመሩ ችለዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመለስ አመልካቾች እየተከራከሩ ያሉት አንድ ዳኛ በሁለት የተለያየ እርከን ባላቸው ፍ/ቤቶች ተሰይመው አንድ ጉዳይ በማየት መወሰናቸው ተገቢነት የለውም የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ይኸው ዳኛ በኋለኛው ፍ/ቤት ሊሰየሙ የቻሉት በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ተፈቅዶላቸው በመሆኑና የሽሪአ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅም ይህንኑ የሚፈቅድ በመሆኑ ዳኛው በሁለቱም ፍ/ቤቶች ተሰይመው ጉዳዩን አይተው መወሰናቸው ተገቢነት ያለው ነው የሚል ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ በክልሉ ከፍተኛ የሽሪአ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይተው የወሰኑት ዳኛ ሼህ አብዱ ሁሴን ጉዳዩ በይግባኝ በቀረበበት በጠቅላይ ሽሪአ ፍ/ቤትም ተሰይመው ጉዳዩን አይተው መወሰናቸው በግራ ቀኙ ክርክር ያልቀረበበት ከዚህ መዝገብ ጋር ተያይዘው በሚገኙት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ በግልፅ የተመለከተ ነጥብ ነው፡፡በመሰረቱ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት በአንድ ሰብሳቢና በሁለት ቃዲዎች የሚያስችል መሆኑ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ 132/1998 አንቀፅ 14(2) የተመለከተ አሰያየምን አስመልክቶ የተቀመጠ መሰረታዊ ድንጋጌ ሲሆን በዚህ አግባብም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ከክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት የሚቀርብለትን የመጨረሻ ውሳኔ ሊያይና ተገቢውን እልባት ሊሰጥ የሚገባው በቅድሚያ የክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት በተሟላ ዳኛ ጉዳዩን አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠቱ ሲረጋገጥና ሶስት ዳኞች የሚሰየሙበት የሠበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ያስቀርባል ካለው በኋላ መሆኑን ያሳያል፡፡

አንድ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ቃዲ ክርክር የተነሣበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት የሚያውቀው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ከችሎት ሊነሳ የሚገባ መሆኑ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ 132/1998 አንቀፅ 17(1)(ሐ) የተመለከተ መሰረታዊ መርህ ሆኖ እያለ በክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር አይተው ለጉዳዩ ተገቢ ነው የተባለውን ውሳኔ ከሁለት የስራ ባልደረባዎቻቸው ጋር ሆነው የሰጡት በተራ ቁጥር 3 የተሰየሙት ዳኛ በክልሉ ከፍተኛ የሸሪአ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይተው የወሰኑ መሆኑ ለግራ ቀኙ ክርክር በክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስቀድመው በሚያውቁና ለጉዳዩ ገለልተኛ ባልሆኑ አንድ የችሎቱ ዳኛ ጭምር መሆኑ በሕግ የተመለከተው የይግባኝ ሰሚ ችሎት የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ ውሳኔው እንደተሰጠ ያረጋግጣል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለበት ፍርድ በይግባኝ ካልተለወጠ የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡ በህግ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ከነግድፈቱም ቢሆን የሰጠው ውሳኔ መከበር እና መፈጸም አለበት፡፡ ይህም አንዱ የህግ የበላይነት መገለጫ ነው፡፡ ነገር ግን በህግ የተቋቋመው የዳኝነት ተቋም በተለየም ከአንድ ዳኛ በላይ ሆኖ በሚሰየምበት ችሎት ከተፈቀደለት የዳኛ ቁጥር በታች ሆኖ ከተሰየመ ህጋዊ እና አስገዳጅ ውሳኔ ለመሥጠት ያለውን የአስገዳጅነት ሀይሉንና የህግ ከለላውን ያሳጣዋል፡፡ በአንድ በተሰየመ ችሎት የተለያየ እና የህግ ዕውቅናና መሰረት የሌለው ውሳኔ እንዲሰጥ ዕድል የሚከፍትና ዜጎች በዳኝነት አካሉ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትም በዚህ ጉዳይ በሰበር መዝገብ ቁጥር 73696 ቅጽ 13 ላይ “የዳኞች ቁጥር ሳይሟላ የሚሠጠው ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ደግሞ እንደተሰጠ የማይቆጠርና ህጋዊ ውጤት ሊኖረው የሚገባ አይደለም” በማለት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ተመሳሳይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም በሰ/መ/ቁ.187862 ተሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የሥነ-ስርዓት ግደፈት ያለበት ውሳኔ ተፈጻሚና የጸና የሚሆነው በተሟላ ችሎት ከተሠጠ ብቻ ነው፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት ተገቢውን የዳኛ ቁጥር በያዘ ችሎት ውሳኔውን አለመስጠቱ መሰረታዊ የክርክር አመራር ስነስርዓት ግድፈት መፈጸሙን የሚያሳይ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከክልሉ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ላይ የሰበር ቅሬታ ሲቀርበለት በቅድሚያ ለሰበር ቅሬታው መሰረት የሆነው ውሳኔ የተሟላ የችሎት ዳኛን በያዘ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠና ሕጋዊ ውጤት ያለው መሆን አለመሆኑን ሊመረምር ሲገባ ይህንን ሳያደርግ ቀርቶ ሚና ትሬዲንግ እና ሞጣ ከተማ የሚገኝ ስኬት ዱቄት ፋብሪካን በተመለከተ ጠቅላይ ሸሪአ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር በዚህ ረገድ የወረዳው የሸሪአ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱና ሌላውን

የጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት በመ.ቁ 59199 በቀን 22/03/2015 ዓ.ም እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 119939 በቀን 24/06/2015 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348 መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ሸሪአ ፍ/ቤት የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን በሕግ አግባብ በተሟላ የችሎት ዳኛ እና በህጉ አግባብ መርቶ የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን መልሠናል፡፡
3. ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ኮፒ ተደርጎ ከሰ/መ/ቁ.245689 ጋር እንዲያያዝ ታዟል፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ</u>፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማ/ት

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም